# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# አካባቢ ጥበቃ እና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን

# የአካባቢ ብክለትና አየር ንብረት ለውጥ ዘርፍ
# የፍኖተ ብልጽግና መሪ እቅድ

( 2013-2022 )

ሰኔ 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## 1.መግቢያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን በአዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፴፮ ንኡስ አንቀጽ ፪፣፬፣፳፣፮ ከተሰጠው ስልጣንና ተግባር መካከል የአካባቢብክለትና የአየርንብረትለውጥ ዘርፍ የሚያሥተባብራቸው እና የሚመራቸው ተግባራት መካከል ውስጥ በዋነኛነት የአካባቢ ጥበቃ ስታንዳርድ ያዘጋጃል፣አካባቢ እንዳይበከል የመከላከያ ስልት ይቀይሳል፣አግባብ ያላቸውን አካላት ከአካባቢ ጥበቃ አንጻር ያስተባብራል፣ከኢንዱስትሪ ፣ከሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚመነጩ ዝቃጭ ፣ተረፈ ምርት ፣ቆሻሻ በህግ መሰረት መወገዱን ይከታተላል ይቆጣጠራል፣ በህግ አግባብ እርምጃ ይወስዳል ፣እንደወሰድ የደርጋል፣ ከተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚመነጩ የድምጽ እና የአየር ብክለት በህግ መሰረት ይቆጣጠራል እርምጃ ይወስዳል እንዲወሰድ ያደርጋል።

በተጨማሪም የማምረቻና የአገልግት መስጫ ተቋማት እና ሌሎች አካባቢ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ አካላት የብክለት መከላከል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል። በተጨማሪም የአማራጭ የሃይል ምንጮችን የመስራት እና የማስተዋወቅ ስራ የተጣለበት ዘርፍ ጭምር ነው።እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ተልእኮዎችን ለማሳካትና ለመተግበር ዘርፉ ከፍተኛ ሃላፊነት ተጥሎበታል።

ይህን ተልእኮ ለማሳካት በሁለተኛው የእድገትና የምንድግና ክንውን ላይ የታዩ ምልካም አፈጻጸሞች እና ድክመቶች የታዩ ሲሆን በተለይ ሃገራዊ ለውጡ ከተመዘገበ በኋላ በነበሩት ሁለት አመታት አመራሩ በዘርፉ ሰፊ የሆነ የልማትና የመልካም አስተዳደር ስኬቶች የሥመዘገበበት አመት እንደነበር ተገምግሟል ።በአጠቃላይ በእቅድ ዘመኑ ዕቅድ የተቀመጡትን ግቦች በአመራር፣ በፈጻሚው፣ በባለድርሻ አካላቱ እና በህዝቡ የላቀ ተሳትፎ ለማሳካት የተደረገው ጥረት የሚያበረታታ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በዚህም በርካታ መልካም ውጤቶችን ማስዝገብ ተችሏል። ከውጤቶቹ ሁሉ በላቀ ደረጃ የሚጠቀሰው የህዝቡን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የተቻለበት መሆኑ ነው።ነገር ግን በአፈጻጸም ሂደት የታዩ ድክመቶች የነበሩ ሲሆን እነዚህ ድክመቶችን በቀጣይ የእቅድ ዘመን እንዳይደገሙ መስራት ይጠበቅብናል።

ዕቅዱ የከተማችንን ነዋሪ የልማት እና የመልካም አስተዳደር ፍላጐት ለማሳካት የከተማውን ነባራዊ ሁኔታን በመዳሰስ እንዲሁም የመሪ ድርጅቱን የብልጽግና የልማት ግቦችን መነሻ በማድረግ የተጀመረውን የለውጥ ጉዞ ፈጣንና ተከታታይ እንዲሆን ማድረግ በሚያስችል፣ ልማትን በሚያረጋግጥ፣ የአገልግሎት አሰጣጥና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በሚፈታ መልኩ የአፈጻጸም አቅጣጫዎች፣ ያሉ መልካም አጋጣሚዎች እና ስጋቶች ፣ የክትልና ድጋፍ ስርአት እና የድሪጊት መርሃ ግብር

ይዞ ተዘጋጅቶ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 2. የዘርፉ የአምስት አመት ከ(2008-2012) የእድገትና ጥራንስፎርሜሽን አመታት አአጻጸም ግምገማ

በከተማዋ የሚደርሰውን የአካባቢ ብከለትን በመከላከል እና በመቆጣጠር ለነዋሪዎቿ ንጹህናጤናማ አካባቢመፍጠር በከተማው ልማትና አካባቢ ተጣጥመው እንዲሄዱ የኮንስትራክሽን ማእድን አውጪ ፕሮጀክቶች ፣አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ የፋብሪካ ፕሮጀክቶች እናየተለያዩ ደረጃ ያላቸው አዳዲስ ፕሮጀክቶች በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሂደት እንዲያልፉ ለማድረ በ5 አመት ውስት 3000 ታቅዶ 3850 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም 78%ነው ፡፡

በአካባቢ ተፅዕኖ ግማገማ ያለፉ ፕሮጀክቶችን ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግና ግብረ-መልስ ለመስጠት 2320 ፕሮጀክቶች ታቅደው የተከናወነው 552 ነው አፈጻጸሙም 24% ነው ለእቅዱ አለመሳካት በቂ የሰው ሃይልና የአደረጃጀት ችግር በመኖሩ ግቡን በሚፈለገው መንገድ ማሳካት አልተቻለም፡፡

ሌላው የተከናወነው ስራ የአካባቢ ብክለትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስርአት ለመዘርጋት የሚያስችሉ 1 የደንብ ማሻሻያ እና 2 መመሪያዎችን አዘጋጅቶ በማጸደቅ ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ የተፈጸመው የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 25/2000 ማሻሻያ በሂደት ላይ ያለ ሲሆን፡፡ ሌላው የጸደቀው የድምጽ ብክለት ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 1/2011 ዓ.ም የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 25/2000 ማስፈጸሚያ ረቂቅ መመሪያ ደንቡ ባለመጽደቁ መመሪያውን ተግባራዊ ማድረግ አልተቻለም ፡፡

የአካባቢ ላብራቶሪ ቡድን የተቋሙን ተልእኮ ለማሳካት በላብራቶሪ የተደገፈ የብክለት ምርመራ ውጤት በወቅቱ ከራሱ ከተቋሙና ከውጪ ለሚመጡ ተገልጋዮች ደረጃውን የጠበቀ ቀልጣፋ የምርመራ አገልግሎት መስጠት ነው፡፡ከመስሪያ ቤቱ ለጥናትና ክትትል ስራዎች እንዲሁም ከውጭ ተገልጋይ የሚመጡ 16000 ናሙናዎችን ተቀብሎ በላብራቶሪ መርምሮ ውጤት ለመስጠት ታቅዶ 5202 ተከናውኗል ከዘርፉ አገልግሎት 3.5 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ1070019 ተከናውኗል ፡፡

የአካባቢ ብክለት ችግሮችን በመለየት፣ሁሉንም ያሳተፈ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የከተማዋን ብክለት መከላከልና ለህብረተሰቡ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት በተመረጡ 10000 አገልግሎት ሰጪእና

የማምረቻ ተቋማት ላይ የክትትልና ቁጥጥር ስራ ለመስራት ታቅዶ 8014 ተከናውኗል አፈጻጸሙም 80.1%ነው፡፡የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ለመፍታት በ5 አመት ውስጥ 2000 ታቅዶ 3108 ቅሬታዎች ተፈትቷል አፈጻጸሙም 108% ነው፡፡ ሌላው የተከናወነው ተግባር ህግ የማስከበር ተግባር ሲሆን አፈጻጸሙም በ300 ተቋማት እርምጃ የተወሰደ ስሆን ከእነዚህ ውስጥ 287ቱ አስተዳደራዊ እርምጃ ሲሆን 3ቱ ግን ህጋዊ እርምጃ የተወሰደባቸው ነው፡፡

በኢነርጂ ዘርፍ አፈጻጸማችን ስንመለከት ለ1,500,000 ሀይል ቆጣቢ ምድጃዎች ለማምረትና ለማሰራጨት ታቅዶ 889894 ሃይል ቆጣቢ ምድጃዎች በ አምስት አመት ውስጥ ተሰራጭቷል፡፡ አፈጻጸሙም 59%ነው፡፡በተጨማሪም የከተማው ነዋሪ ሃይል ቆጣቢና አማራጭ የሀይል ምንጮችን እንዲጠቀም በየአመቱ 15 ሞዴሎች እና 15 ሰርቶ ማሳያ ጣቢያዎች በመገንባት የማስተዋወቅ፣ የማሻሻል፣ የማላመድና ቴክኖሎጂውን የማሸጋገር ስራ መስራት፤በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር ስር የሚገኙ መ/ቤቶች በሙሉ ሃይል ቆጣቢ አምፖል(CFL) እንዲጠቀሙ ለማድረግ ታቅዶ 7 ተቋማት ብቻ ተተቃሚ ሁነዋል አፈጻጸሙ በጣም ዝቅተኛ ፡፡የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ ግንባታና አጠቃቀም ላይ ጥናት ለማድረግ እና የማሻሻያ ሃሳብ ለማቅረብ 1 ታቅዶ 1 ተከናውኗል፡፡

ለአዲስ አበባ ከተማ የተዘጋጀውን ‹‹ የአየር ንብረት ለውጥ የሚቋቋም አረንጓዴ የኢኮኖሚ (climate resilient green economy) እና የተቀናጀ የአየር ንብረት ለውጥ ለማስተግበር የሚያስችል የልማት እስትራቴጂ ሰነድ አፀድቆ ወደ ተግባር ለማስገባት የተዘጋጀው የከተማዋ አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስልትን እንዲተገበር ለማድረግ ሰነድ በማዘጋጀት እና የትግበራ ማኑዋል በማዘጋጀት ከከተማ ሴክተር ቢሮዎች ከተውጣጡ ጋር ውይይት በማድረግ እና እቅዱ እንዲጸድቅ ተደርጓል፡፡ የተዘጋጀው የከተማዋ አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስልት እንዲተገበር በከተማ ባለድርሻ በሆኑ ሴክተር ቢሮዎች አሃድ በማቋቋም በሚፈለገውም ደረጃ ባይሆንም አቅደወደው ወደተግባር ተገብቷል ፡፡የከተማዋን ከባቢያዊ ነባራዊ ሁኔታና ወደፊት የሚያጋጥማትን ለውጥ የሚያመላክቱ 2 ሰነዶች (city's state of the environment and environmental outlook) በማዘጋጀት፤በሁለት ሰነዶቹ ዝግጅት ላይ የቢሳተፉ የባለድረሻ አካላት ባለሙያዎች የግንዛቤ ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል ፡፡ ሌላው የተከናወነው አበይት ተግባር በከተማዋ ለአየር ብክለት መንስኤ የሆኑትን ንጥረ ነገሮች መጠንና አይነታቸውን የሚጠቁም የአየር ብክለት መቆጣጠሪያ ጣቢያ ማቋቋም እና የከተማዋ የአየር ጥራት መቆጣጠሪያ ስርዓት እንዲዘረጋ ለማድረግ ታቅዶ፡ በከተማው ባሉ አምስት አካባቢዎች ማለትም (በቆሼ ላንድ ፊል፣ ፒያሳ፣ መርካቶ ፣ሜክሲኮ እና ኮሚሽን መስሪያቤት ግቢ ውስጥ) ተተክሎ መረጃ እየተሰበሰበ ፡፡

G-SCAN/computer controlled car gas analayzer/ ይህን መሳሪያ በመጠቀም በተለይ የመኪና ጭስን የመለካት ስራው ተካናውኗል መረጃውም እየተተነተነ ይገኛል፡፡ለአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ የሚሆኑ ጋዞች ልቀት መጠን አንድ ጊዜ በከተማዋ የከተየሙቀት ልኬት ( inventory) በማከናወን መረጃውን የማደራጀት ስራ በ C-40 ግሩፕ ድጋፍ ተደርጓል፡ቀጥሎ የተከናወነው ስራ መረጃ የመሰብሰብ እና የመተንተን ስራ ሲሆን በካይ ጋዝ ከሚለቁ ዘርፎች/ተቀማት የ2016 መረጃን በመጠቀም መረጃው ተተንትል፡፡በዚህም መሰረት በአዲስ አበባ 1116195 ቶን $CO_2$ ወደ ከባቢ እንደሚለቀቅ መረጃዎች ያመላክታሉ ድርሻቸውን ስንመለከት ከትራንስፖርት ዘርፍ 78%!ከደረቅ ቆሻሻ 13% ! (ከመኖሪያ ከንግድ ከትላልቅ አምራች እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት 8%)! ከከተማ ግብርና ዘርፎች 1% ነው፡፡የጋዙን መጠን ለመቀነስ የሚያሥችል ስራዎች ባለድርሻ አካላት አቅደው ወደትግበራ እየገቡ ይገኛሉ፡፡ ባጠቃላይ በአምስት

አመታት ውስጥ የታዩ ጥንካሬዎች እና ድክመጦችን በመለየት ጥንካሬዎችን ማስቀጠልና ድክመቶችን ማረም ይገባናል፡፡

## 3. በዘርፉ የነበሩ ጥንካሬዎች እና ድክመቶች

| ጠንካራ ጎኖች | ደካማ ጎኖች |
|---|---|
| • ያልተማከለ አደረጃጀት መፈጠሩ<br>• የግልጽነትና የተጠያቂነት አሰራር መዘርጋቱ<br>• ብክለትን ለመከላከል የሚያግዙ መመሪያ እና ደንቦች መኖራቸው<br>• እስከ ወረዳ ድረስ አደረጃጀት መዘርጋቱ<br>• በሰው ሃይል አቅም ግንባታ ላይ ትኩረት እየተደረገ መሆኑ<br>• የተለያየ የሙያ ስብጥር ያላቸው እንዲሁም በአቅም በአመለካካት መሻሻል ያሳዩ ባለሙያዎች መኖር<br>• በርካታ ወጣቶች ወደዘርፉ እንዲቀላቀሉ በደረጉ<br>• ለፕሮጀክቶች እና ለስራ ማስኪያጃ የሚመደበው በጀ እያደገ መምጣቱ<br>• ከአገልግሎት ገቢ የመሰብሰብ አቅማችን እያደገ መምጣቱ | • በሁሉም እርከን የተቀናጀ አመራር አለመኖር<br>• የተቀናጀ የክትትልና የግምገማ ስርአት አለመኖር<br>• ለህዝቡ የዘርፉን መመሪያ እን ደንቦች ያለማስገንዘብ ችግር<br>• ብልሹ አሰራርን በተግባር የሚዋጋ ህብረተሰብ በበቂ መጠን ያለመኖር<br>• የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳን ለማረጋገጥ የተሰሩ ስራዎችን ዉጤት ለመለካት የሚያስችል የአቅም ዉስንነት መኖር፣<br>• የተቀናጀ የእቅድ አፈጻጸም ስልት እና ግምገማ ያለመኖር<br>• ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርአት አለመዘር<br>• የመዋቅር መለዋወጥ እና የተረጋጋ አመራር<br>• ብቃት ያላቸውን ሰራተኞች ሊስብ የሚችል የክፍያ ስርአት ያለመኖር<br>• በመዋቅሩ መሰረት የተሟላ የሰው ሃይል አለመኖር<br>• የተፈቀደን በጀት በአግባቡና በወቅቱ መጠቀም አለመቻል<br>• የግዥ ስርአቱ የተንዛዛ እና ፍላጎትን የሚያሟላ አለመሆን<br>• የበካይ ነገሮች መጠንና አይነት መጨመር እና ከዚህ ሊከስት የሚች\|ውን አለታዊ ተፅዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ የቴክኖልጂ፤ፊይናንስና የተክኒካዊ አቅም ዉስንነት ማጋጠሙ |

## 4.በዘርፉ ያጋጠሙ ፈተናዎች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች

| ያጋጠሙ ፈተናዎች | የተወሰዱ መፍትሄዎች |
|---|---|
| • የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ በአግባቡ ያለመወገድ ችግሮች<br>• ኢንድስትሪዎች እና ተቋማት ብክለታቸውን ሳያጣሩ ማስወገድ<br>• ሰላም የሚነሳ የድምጽ እና የሽታ ብክለት መኖር<br>• የእይታ ብክለት ችግር መኖር<br>• የከተማ ብክለት መባባስ<br>• ስራና ሰላማዊ ኑሮን መረበሽ<br>• የከተማ ውበት መቀነስ | • የማህበረሰቡን የአካባቢ እንክብካቤ ግንዛቤ መፍጠርና ተሳትፎን ማሳደግ<br>• የአካባቢ /የአየር የድምጽ የጨረር የሽታ የወንዞች ብክለትን ለመቀነስ እና ለመከላከል የህግ ማእቀፍ እና የአሰራር ስርዓት መዘርጋት<br>• ከፋብሪካዎች እና ከኢንዲሱትሪዎች የሚወጣ ቆሻሻና ፍሳሽ በአመንጭው አካል በአግባቡ የሚወገዱበትን ስልትመቀየስ እና ተግባራዊ እንዲደረግ ተገቢውን ክትት ማደረግ<br>• ከፋብሪካ እና ከመኖሪያ አካባቢዎች እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚወጣ ደረቅና ፍሳሽ በአግባቡ መሰብሰብ እና የመልሶ መጠቀም ስልት መቀየስ |

## 5. በዘርፉ የነበሩ መልካም አጋጣሚዎች እና መልካም ተሞክርዎች

| የነበሩ መልካም አጋጣሚዎች | የነበሩ መልካም ተሞክርዎች |
|---|---|
| • በዘርፉ የሚዘጋጁ ስትራቴጂዎች እናእቅዶች<br>ከሃገሪቱ የልማት እቅዶች ተጣጥሞ ተግባራዊ<br>እንዲሆኑ መደረጋቸው እና የአመራር ክትትሉ እያደገ መምጣጡ<br>• በዘርፉ የሚከናወኑ ስራዎች በምርምርና እና በፈጠራ ስራዎች<br>እንዲደገፉ እየተደረገ መሆኑ<br>• ኢነርጂ ቆጣቢ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች እየተበራከቱ መምጣጣቸው<br>• በቴክኖሎጂ የተደገፈ የብክለት ክትትልና ቁጥጥር ስራ መሰራቱ፡፡<br>• በከተማ ደረጃ የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም አረንጓዴ ኢኮኖ<br>ስትራቴጂ ተግባር | • የአቅም ግንባታና የልምድ ልውውጥ በሃገር ውስጥና ከሃገር<br>ውጪ መኖር<br>• ከከፍተኛ የጥምህርት ተቋማት ጋር ስራዎችን በጥናት ለመደገፍ<br>እየተሰራ መኖር<br>• የሚዲያ አካላት እና ባለሃብቶች ስለአየር ንብረት ለውጥ<br>በጅምር ደረጃም ቢሆን ተገንዝበው ወደስራ መግባታቸው<br>• በአትዮጵያ ደረጃ ኤጀንሲ የአካባቢ ላብራቶሪዉ አክሬድት<br>አንዲደረግ ተቋሙ ትኩረት መስጠቱ |

## 6.የልማት ዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች፣

- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዳ ኢኮኖሚ ስሌት በአገሪቱ የልማት እቅድ ውስጥ እንዱካተት (mainstreaming) እና እንዱተገበር ማድረግ፣
- ከዘርፎች የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂ ጋዝች ልቀት መጠን መቀነሱን ማረጋገጥ
- በህብረተሰቡ ላይ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ የመቋቋም አቅም እንዱጎለብት በትኩረት መስራት፣
- የአካባቢ ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስችለሉ ሥርዓቶችን የመዘርጋት እና እንዲተገበሩ የሚያስችሉ ተግባራትን በትኩረት መስራት፣

## 7.የኮሚሽኑ ራዕይ

አዲስ አበባ በ2022 ዓ.ም ከብክለት ነፃ የሆነች ከአካባቢ ጋር የተጣጣመ ልማት እና አረንጓዴነቷ የተጠበቀ ንፁህ እና ጤናማ አካባቢ የተፈጠረባት በተምሳሌት ከሚጠቀሱት የአፍሪካ ከተሞች አንዷ ሆኖ ማየት

## 8. እሴት

ኮሚሽኑ በሚያከናውናቸው ማናቸውም አስተዳደራዊና ልማታዊ ስራዎችን ለማከናወን በአመራሩና በሰራተኛው ተግባር ላይ የሚያውላቸውና መለያው የሆኑትን ጠንካራ እሴቶችን በመያዝ ሲሆን እነዚህም ፡-

- ተጠያቂነት
- ለለውጥ ዝግጁነት
- የላቀ አገልግሎት መስጠት
- በእውቀትና በእውነት መምራትና መስራት
- ለፍትህና ለህግ የበላይነት በጽናት መታገል
- መልካም የስራ ግንኙነት መፍጠርና ለጋራ አላማ መቆም ናቸው፡፡

## 9 ተልእኮ

አዲስ አበባ ከተማን የህዝቡን ግንዛቤ እና ተሳትፎን በማሳደግ በወቅታዊ ቴክኖሎጂና በአካባቢ ህጎች የታገዘ የብክለት ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ልማትን ከአካባቢ ጋር በማጣጣም የአየር ንብረትየአየር ንብረት ተጽኖን በማላበድ እንዲሁም ዘላቂ የተፈጥሮ ሃብት አያያዝና አጠቃቀምን በማሳደግ የከተማዋን ነዋሪዎች በንፁህ እና ጤናማ አካባቢ የመኖር መብቱ እንዲከበር ማድረግ፡፡

## 10 .ዋና ዓላማ

የአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂን በመተግበርና ከአገር በቀል ኢኮኖሚ ልማት ዕቅዱ ጋር በማጣጣም የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን እና ብክለት በመቀነስ የአካባቢ ደህንነትን በመጠበቅ ዘላቂ አገራዊ ልማትና እድገትን ማረጋገጥ፡፡

የዘርፉ ልማት ዕቅድ ዝርዝር ዓላማዎች የሚከተለት ናቸዉ፡-

ዓላማ 1፡- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂን በመተግበርና ከአገር በቀል ኢኮኖሚ ልማት ዕቅድ ጋር በማጣጣም የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን በመቀነስ ዘላቂ ልማትና እድገትን ማረጋገጥ፣

ዓላማ 2.በከተማዋ የሚደርሰውን የአካባቢ መበከል/መጎሳቆልን በግንዛቤ፣ በላቦራቶሪ ምርመራና ህጎች በመታገዝ በመከላከል እና በመቆጣጠር ለነዋሪዎቿ ንጹህና ጤናማ አካባቢ መፍጠር

ዓላማ 3. የመረጃና ቴክኖሎጂ አቅርቦትና መሰረተልማት በማሳደግ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት

### ዓላማ 1፡- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂን በመተግበርና ከአገር በቀል ኢኮኖሚ ልማት ዕቅድ ጋር በማጣጣም የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን በመቀነስ ዘላቂ ልማትና እድገትን ማረጋገጥ፣

**ግብ 1. የዘርፍ መ/ቤቶች ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ትግበራ ሜይንስትሪም ያደረጉ መሆኑን እና ውጤታማነታቸውን ማረጋገጥ፡፡**

በከተማዋ ውስጥ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ ተፅዕኖ የሚያደርሱም ሆነ የሚደርስባቸውን ተቋማት በመለየት በቅነሳውና አደጋውን በመቀነስ ዘርፍ የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ በዕቅዳቸው በማካተት እንዲተገብሩት ይደረጋል፡፡ ዕቅዳቸውን እየተገበሩ ስለመሆናቸው በክትትልና ሪፖ
ርት መረጃው ይሰበሰባል፡፡

አዲስ አበባ ከተማ በምታካሄደው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ሥራዎች ተቋማት የሚያመነጩት እና ወደ አካባቢ የሚለቀቁትን የሙቀት አማቂ ጋዞች መጠን በስታንዲርደ መሠረት መረጃዎችን በማሰባሰብ እና በማደራጀት አሁን ካለው 3.6 ሚ.ቶን (3.6 MtCO2eq.) የቅነሳ መጠን በዕቅዱ ዘመኑ መጨረሻ 13.9 ሚ.ቶን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት የመቀነስና መቀነሱን የማረጋገጥ ስራ የሚሰራ ሲሆን በሴክተር መስሪያ ቤቶቹ የሚቀነሰዉን የቅነሳ መጠን በተመለከተ ዝርዝሩ እንደሚከተለዉ ቀርቧል

| ተ/ቁ | የዘርፍ ስም | የሚቀነሰዉ የሙቀት አማቂ ጋዞች ሌቀት መጠን | | ፈፃሚ ተቋም | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | መለኪያ | በ2022 የሚደረስበት የቅነሳ መጠን | | |
| 1 | ኢነርጂ(ከመኖሪያ ቤቶች፡ ከተቋማት እና ከማምረቻ) | tCO2 | 40,324.13 | አዲስ አበባ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን | |
| 2 | ትራንስፖርት | tCO2 | 13,789,099.8 | አዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ፣ አየር መንገድ፤አዲስ አበባ ቀላል ምድር ባቡር ኢንተርፕራይዝ | |
| 3 | ከደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ | tCO2 | 54,804.64 | አዲስ አበባ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ እና ዉሃና ፍሳሽ ባላስልጣን | |
| ጠቅላላ ድምር | | tCO2 | 13,884,228.6 | | |

**ግብ 2. የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን ለመቋቋም የሚረዱ 10 የአረንጓዴ ቴክኖሎጅዎችን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን መለየት፣ የማስተዋወቅና የማሸጋገር ተግባራት እንዲተገበሩ የማድረግ ሥራዎች ይሠራሉ፡፡**

በአየር ንብረት ለውጥ የአማቂ ጋዞችን ልቀት ለመቀነሳም ሆነ የሚደርሰውን ተፅዕኖ ለመቋቋም የሚረዱ በተለያዩ አካላት የሚቀርበውን አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እንዲዘጋጁ የማበረታታት፣ እውቅና መስጠት፣ ማስተዋወቅና የተለያዩ ድጋፎችን የማድረግ ሥራ ይሰራል፡፡

ለአየር ንብረት ለውጥ የማጣጣሚያና የስርየት እርምጃዎችን ለመውሰድ አጋዥ የሆኑ የድጋፍ ምንጮችን መለየትና ግንኙነት መፍጠር፣ በአካባቢና አየር ንብረት ለውጥ ዙሪያ ሀብት የሚያስገኙ ፕሮጀክቶችን ማዘጋጀትና ለድጋፍ ሰጪዎች ማቅረብ

**ግብ 3 .የከተማው ነዋሪ ሃይል ቆጣቢና አማራጭ የሀይል ምንጮችን እንዲጠቀም በየአመቱ 5 ሞዴሎች እና 5 ሰርቶ ማሳያ ጣቢያዎች በመገንባት የማስተዋወቅ፣ የማሻሻል፣ የማላመድና ቴክኖሎጂውን የማሸጋገር ስራ መስራት፤**

በዚህ ስራ 1,500,000 ሀይል ቆጣቢ ምድጃዎች ለማምረትና ለማሰራጨት እንዲቻል በስራው ላይ ለተሰማሩ ግለሰቦች ፣ድርጅቶች ፣ ማህበራት የቴክኒክ እገዛና ድጋፍ ይሰጣል፤

**ዓላማ 2.በከተማዋ የሚደርሰውን የአካባቢ መበከል/መጎሳቆልን በግንዛቤ፣ በላቦራቶሪ ምርመራና ህጎች በመታገዝ በመከላከል እና በመቆጣጠር ለነዋሪዎቿ ንጹህና ጤናማ አካባቢ መፍጠር**

**ግብ 1. በአካባቢ ዘርፍ የህግ ማዕቀፎች አሁን ካለው 8 ህጎች በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 20 የሚሆኑ የተለያዩ የአካባቢ መንከባከቢያ ስርዓቶች ተዘጋጅተው እንዲተገበሩ ማድረግ**

አሁን በመተግበር ላይ የሚገኙ የአካባቢ መበከል/መጎሳቆልን ለመከላከል የሚያስችሉ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ደረጃዎች፣ ጋይድላይኖች አተገባበር እየታየ የማሻሻልና አዳዲስ የማውጣት ስራዎች ይከናወናሉ

**ግብ 2. በዘርፉ ለሚከናወኑ የተለያዩ ሥራዎች የህብረተሰቡን ግንዛቤ ሊያሳድጉ የሚችሉ ስራዎች ለመስራት በዕቅዱ ዘመኑ ለ250,000 ለሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍልች በዘርፉ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ መፍጠር**

በአካባቢ ብክለት፣ በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ፣ በአየር ንብረት ለውጥ፣ በታዳሽ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና በመሳሰሉት የፅንሰሃሳብ፣ አስፈላጊነትና አተጋባበር እንዲሁም በአካባቢ ህጎች ላይ ግንዛቤ ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት፣ የህብረተሰብ ክፍሎችና ለነዋሪው የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የማስተማር ስራ ይሰራል። ለዚህ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ማሟላትና የግንዛቤ ሥራውን ውጤት የመዳሰስ ተግባር ይከናወናል።

**ግብ.3 ፦ በየአመቱ ለ2400 ማምረቻና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እና ለ500 የብክለት ይወገድልኝ አቤቱታዎችን ተቀብሎ ምላሽ በመስጠት! የብክለት ቁጥጥር ሽፋኑን ማስፋት! ብክለት ባደረሱ 275 ተቋማት ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ እንዲሰድ እን ህጋዊ ጉዳዮች ላይ ክትትል በማድረግ የአካባቢ ደረጃ ማስከበር።**

በከተማዋ የሚገኙ የማምረቻና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ በአካባቢ ላይ ስለሚያደርሱት ብክለት ክትትል የሚደረግ ሲሆን ከህብረተሰብ የሚቀርቡ የብክለት ይወገድልኝ አቤቱታዎችን ተቀብሎ ምላሽ የመስጠት ሥራ ይከናወናል። በዚህ ወቅትም ጥፋተኛ ሆነው በሚገኙ ተቋማት ላይ በላቦራቶሪና ሌሎች መሳሪያዎች ጭምር በማረጋገጥ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ ይወሰዳል።

**ግብ.4. ከመስሪያ ቤቱ ለክትትል ስራዎች እንዲሁም ከውጭ ተገልጋይ የሚመጡ 15,000 ናሙናዎችን ተቀብሎ በላብራቶሪ መርምሮ ውጤት በመስጠት ለሚፈለገው አላማ እንዲውል ማድረግ እና ከዘርፉ አገልግሎት 5 ሚሊዮን ብር መሰብሰብ።**

**ግብ 5. በከተማዋ ልማትና አካባቢ ተጣጥመው እንዲተገበሩ በማድረግ ለነዋሪዎቿ ንፁሕና ጤናማ አካባቢ ለመፍጠር በ7000 የማምረቻና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አዳዲስ ፕሮጀክቶች ከአካባቢ አንፃር ተገምግመው በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሂደት እንዲያልፉ እና በ880 ነባር ተቋማት የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ እንዲያቀርቡ ማድረግ፤**

ግብ 6. በአካባቢ ተፅዕኖ ግማገማ ያለፉ ፕሮጀክቶችን ክትትልና ቁጥጥር ሥራ 1100 የማምረቻና የአገልግሎት ሰጪዎች ላይ ማድረግና የተመረጡ 50 ተቋማት የአካባቢ ኦዲት እንዲያቀርቡ ማድረግ

**ዓላማ 3. የመረጃና ቴክኖሎጂ አቅርቦትና መሰረተልማት በማሳደግ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት**

ግብ 1. የከተማዋን ከባቢያዊ ነባራዊ ሁኔታና ወደፊት የሚያጋጥማትን ለውጥ የሚያመላክት ሰነድ (city's state of the environment) መረጃዎችን በማሰባሰብና በማደራጀት ማዘጋጀት፤

ግብ 2፡ በከተማዋ ለአየር ብክለት መንስኤ የሆኑትን ንጥረ ነገሮች መጠንና አይነታቸውን የሚጠቁም የአየር ብክለት መቆጣጠሪያ ጣቢያ ቁጥር ወደ 15 ማሳደግ እና በማጠናቀር መረጃውን ተደራሽ ማድረግ

ግብ 3. የአካባቢ ላቦራቶሪው የሚጠበቅበትን አገልግሎት እንዲሰጥ በመሳሪያ፣ በኬሚካል፣ በብቁ የሰው ሃይል በማደራጀትና ደረጃውን የጠበቀ አሰራር በመዘራጋት አቅም ማሳደግ

ግብ 4. በከተማዋ የሚገኙ የማምረቻና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚገኙበትን ቦታ፣ ተግባራቸውን፣ የብክለት ደረጃና ለውጡን የሚመለከቱ እንዲሁም በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ያለፉና ያላለፉ ፕሮጀክቶች ሁኔታ የሚያመላክት የመረጃ ቋት ማደራጀት፡፡

## የክትትል፣ የግምገማና ድጋፍ አግባብ እና የአፈጻጸም አቅጣጫዎች

- ለእቅዱ ተፈጻሚነት ማረጋገጫ የድጋፍና ክትትል እቅድ ማዘጋጀትና በዕቅዱ መሠረት መፈጸም፣
- ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በየወቅቱ በሚደረገው የጋራ ምክክር መድረክ ላይ እንደ አንድ አጀንዳ ተወስዶ የአፈጻጸም ግምገማና የቀጣይ ድርጊት ነጥቦች ተለይተው በባለቤትነት እንዲፈጸሙ ማድረግ፣ (በሪፖርት ላይ የሚሰጥ የጽሁፍ ግብረመልስ፣ በመድረክ የሚደረግ ድጋፍ፣ በአካል ተገኝቶ በሚደረግ የክትትልና ድጋፍ፣ በምልከታ ወይም የሱፐርቪዥን ድጋፍ ዘርዝሮ በማቀድ መተግበር ይኖርበታል፡
- የኮሚሽኑ የበላይ አመራር የወጣውን እቅድ በጥብቅ ዲሲፕሊን የሚመራበትን ሁኔታ አመቻችቶ ይንቀሣቀሣል፡፡
- በዘርፋችን የሚተላለፉ መልእክቶች የታለመላቸውን ግብ በማሣካት ነዋሪውን ለፈጣንና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ማነሣሣታቸውን ይከታተላል፡፡
- ዘርፉ በስሩ ዘርፎችን እና ባለድርሻ አካላት ተደጋግፈው እቅዱን ለማሣካት ያስችላቸው ዘንድ በመደበኛ የግንኙነት ወቅት እቅድ አፈፃፀምን ዋነኛ አጀንዳ አድርጎ የመገምገም፣ የድጋፍ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

- ዘርፉ የአፈፃፀም መልካም ልምዶችን በማስፋት በመደበኛነት የተቀራረበ አፈፃፀም ይሰራል፡፡